# የገንዘብ ሚኒስቴር

## የኮረና ቫይረስ ወረርሽኝ በታክስ ከፋዩ የሥራ እንስቅስቃሴ ላይ ያደረሰዉን ጫና ለመቀነስ የወጣ መመሪያ ቁጥር 249/2013

ገንዘብ ሚኒስቴር

ግንቦት 2012 ዓ.ም

# የኮረና ቫይረስ ወረርሽኝ በታክስ ከፋዩ የሥራ እንቅስቃሴ ላይ ያደረሰውን ጫና ለመቀነስ የወጣ መመሪያ ቁጥር 249/2013

1. **አውጪው ባለሥልጣን**

የገንዘብ ሚኒስቴር በፌደራል የታክስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 983/2008 እና በአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ቁጥር 3/2012 ማስፈፀሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ይህንን መመሪያ አውጥቷል፡፡

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ ድንጋጌዎች

2. **አጭር ርዕስ**

ይህ መመሪያ "የኮረና ወረርሽኝ በታክስ ከፋዩ የሥራ እንቅስቃሴ ላይ ያደረሰውን ጫና ለመቀነስ የወጣ መመሪያ ቁጥር 249/2013" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

3. **ትርጓሜ**

በፌደራል የታክስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 983/2008 ወይም በፌደራል የገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 979/2008 ትርጉም የተሰጠው ቃል በዚህ መመሪያ ወስጥ ጥቅም ላይ የዋለ እንደሆነ በታክስ አስተዳደር አዋጁ ወይም በገቢ ግብር አዋጁ የተሰጠውን ትርጉም ይይዛል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ወስጥ፣

ሀ) "የመንግሥት ውሣኔ" ማለት በኮረና ቫይረስ ወረርሽኝ ምክንያት ጉዳት የደረሰበት ታክስ ከፋይ እንዲሁም ሌላው የህብረተሰብ ክፍል ያጋጠመውን የኑሮ ጫና ለመቀነስ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ሚያዝያ 16 ቀን 2012 ያስተላለፈው ውሣኔ ነው፡፡

ለ) "ሚኒስቴር" ወይም "ሚኒስትር" ማለት እንደቅደምተከተሉ የገቢዎች ሚኒስቴር ወይም ሚኒስትር ነው፡፡

ሐ) "የገቢ ግብር አዋጅ" ማለት የገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 979/2008 ነው፡፡

መ) "የተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ" ማለት የተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ ቁጥር 285/1994 (እንደተሻሻለ) ነው፡፡

ሠ) "የተርንኦቨር ታክስ" ማለት የተርንኦቨር ታክስ አዋጅ ቁጥር 308/1995 (እንደተሻሻለ) ነው፡፡

## ክፍል ሁለት

## ኪሣራን ስለማሸጋገር

## 4. ኪሣራ የሚሸጋገርበት ሁኔታ

1/ በገቢ ግብር አዋጅ የተደነገገው ቢኖርም ማናቸውም ታክስ ከፋይ ለሁለት የግብር ዓመታት ያገጠውን ኪሣራ የማሸጋገር መብቱን የተጠቀመበት ቢሆንም ባይሆንም፣ በ2012 የግብር ዓመት (በአውሮፓውያን የሂሳብ ዓመት ሂሳባቸውን ለሚዘጉ በ2020 የግብር ዓመት) ያጋጠመው ኪሣራ ለወደፊት ከሚያገኘው ግብር የሚከፈልበት ገቢ ጋር እንዲካካስ ይደረጋል፡፡

2/ በታክስ ከፋዩ የሥራ ዘመን እንዲሸጋገር የተደረገው በአንድ የግብር ዓመት የደረሰ ኪሣራ ብቻ ከሆነ በ2012 የግብር ዓመት ያጋጠመው ኪሣራ እንዲሻገር የተደረገ ቢሆንም ለወፊት የአንድ ተጨማሪ የግብር ዓመትን ኪሣራ የማሸጋገር መብት ይኖረዋል፡፡

3/ በታክስ ከፋዩ የሥራ ዘመን እንዲሻገር የተደረገ ኪሣራ የሌለ ከሆነ በ2012 የግብር ዓመት ያጋጠመው ኪሣራ እንዲሸጋገር የተደረገ ቢሆንም ወደፊት በተጨማሪነት ለሁለት የግብር ዓመታት ያጋጠመው ኪሣራ እንዲሸጋገር ይደረጋል፡፡

4/ የገቢ ግብር አዋጅ ሥራ ላይ ከመዋሉ በፊት በነበረ የግብር ዓመት ያጋጠመ ኪሣራ ለ3 ተከታታይ ዓመታት ከተገኘ ግብር የሚከፈልበት ገቢ ጋር ሊካካስ የሚችል ሲሆን፣ ያልተካካሰ ቀሪ ኪሣራ ቢኖር ሊካካስ አይችልም፡፡ ታክስ ከፋዩ በተከታታይ የግብር ዓመታት ኪሣራ ያጋጠመው ከሆነ ኪሣራው ሊካካስ የሚችለው የቀደመው ኪሣራ ሊካካስ የሚችልበት ጊዜ ከተጠናቀቀ በኋላ ባሉት ተከታታይ 3 የግብር ዓመታት ከተገኘ ግብር የሚከፈልበት ገቢ ጋር ይሆናል፡፡

5/ የገቢ ግብር አዋጅ ሥራ ላይ ከዋለበት ጊዜ ጀምሮ ባሉ የግብር ዓመታት ያጋጠመ ኪሣራ ለ5 ተከታታይ ዓመታት ከተገኘ ግብር የሚከፈልበት ገቢ ጋር ሊካካስ የሚችል ሲሆን፣ ያልተካካሰ ኪሣራ ወደ ቀጣይ የግብር ዓመት ሊተላለፍ አይችልም፡፡

6/ ታክስ ከፋዩ የገቢ ግብር አዋጅ ሥራ ላይ ከመዋሉ በፊት እንዲተላለፍለት የተደረገው አንድ ኪሣራ ብቻ ከሆነ የገቢ ግብር አዋጅ ሥራ ላይ ከዋለ በኋላ የሚያጋጥመውን ተጨማሪ የአንድ የግብር ዓመት ኪሣራ የማሸጋገር መብት ይኖረዋል፡፡

## 5. ሪፖርት ስለማቅረብ

ሚኒስቴሩ በመንግሥት ውሣኔ መሠረት እንዲሸጋገር የተደረገውን የ2012 የግብር ዓመት ኪሣራ ለይቶ በመመዝገብ ለገንዘብ ሚኒስቴር ሪፖርት ማድረግ አለበት፡፡

## ክፍል ሦስት

## የተጨማሪ እሴት ታክስና የተርንኦቨር ታክስ የሚከታወቂያ እና የመክፍያ ጊዜ ስለማዘግየት

## 6. የሚስታወቂያ እና የመክፈያ ጊዜ

1/ በተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ እና በተርንኦቨር ታክስ አዋጅ የተደነገገው ቢኖርም ገቢያቸውን በየወሩ አስታውቀው የሚከፍሉ የተጨማሪ እሴት ታክስ እና የተርንኦቨር ታክስ ከፋዮች በመጋቢት፣ ሚያዝያ እና ግንቦት ወራት 2012 ዓ.ም. የሰበሰቡትን የተጨማሪ እሴት ታክስ እና የተርንኦቨር ታክስ በሰኔ ወር 2012 ሊከፍሉ ይችላሉ፡፡

2/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት የሚስታወቂያ እና የመክፈያ ጊዜው በማዘግየቱ ምክንያት ወለድና መቀጫ አይከፈልም፡

3/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተመለከተው ገቢያቸውን በየሦስት ወሩ አስታውቀው የሚከፍሉትን የተጨማሪ እሴት ታክስና የተርንኦቨር ታክስ ከፋዮች የሚከፍሉትን አይጨምርም፡

## 7. የሚኒስቴሩ ኃላፊነት

በዚህ መመሪያ አንቀጽ 6 በተመለከተው መሠረት ለመፈፀም እንዲቻል ሚኒስቴሩ በኮምፒውተር ሲስተም የሚታየው መቀጫ ወለድ በመመሪያ ቁጥር 137/2010 አንቀጽ 7(7) እና 11(2) መሠረት የሚሰበሰብ ስለማይሆኑ ማለጫ በማፍ ከሲስተሙ እንዲሠረዝ ማድረግ አለበት፡፡

# ክፍል አራት

## ለበጎ አድራጎት ዓላማ የሚደረጉ ስጦታዎች

## 8. በወጪ ተቀናሽ ስለማድረግ

1/ በገቢ ግብር አዋጅ የተደነገገው ቢኖርም ታክስ ከፋዮች የኮረና ቫይረስ የሚያደርሰውን ጉዳት ለመቀነስ መንግሥት የሚያደርገውን ጥረት ለማገዝ የሚያደርጉትን የገንዘብ ድጋፍ ግብር ከሚከፈልበት ገቢ 20% (ሃያ በመቶ) ባልበለጠ ማጠን በወጪ ተቀናሽ ማያዝ ይችላሉ፡፡

2/ የዚህ ዓይነቱ የገንዘብ ድጋፍ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ከተደነገገው ማጠን ሳያልፍ እንደሚኖራቸው ለንግድ ሥራው ገቢ ለማስገኘት እንደተደረገ ወጪ በወጪነት ይያዛል፡፡

## 9. የአቀናነስ ሥርዓት

በዚህ መመሪያ የተመለከተው እንደተጠበቀ ሆኖ የታክሱ ባለሥልጣን በገቢ ግብር አዋጅ እና ይህንኑ አዋጅ ለማስፈፀም በወጣው ደንብ እንዲሁም ስለተቀናሽ ወጪዎች በወጣው መመሪያ ቁጥር 5/2011 የሚቀርቡ ማስረጃዎችን በመመርመር ተቀናሹን ይፈቅዳል፡፡

# ክፍል አምስት

## የግል የንግድ ድርጅቶች የጡረታ መዋጮ

## 10. የጡረታ መዋጮ ክፍያን ስለማዘግየት

1/ በግል ድርጅቶች ሠራተኞች የጡረታ አዋጅ ቁጥር 715/2003 አንቀጽ 11 የግል የንግድ ድርጅቶች የተማለከተው ቢኖርም በአዋጁ መሠረት ለሠራተኛው ጡረታ በማቢት፣ በሚያዝያ እና በግንቦት ወራት 2012 ሊያደርጉት የሚባውን የጡረታ መዋጮ በሰኔ ወር 2012 ገቢ ሚድረግ ይችላሉ፡፡

2/ የግል የንግድ ድርጅቶች የጡረታ መዋጮውን አዘግይተው በመክፈላቸው ወለድና መቀጫ እንዲከፍሉ አይጠየቁም፡፡

**14. <u>መመሪያው የሚጸናበት ጊዜ</u>**

ይህ መመሪያ ከግንቦት 11 ቀን 2012 ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

***አዲስ አበባ ግንቦት 10 ቀን 2012 ዓ.ም.***

***አህመድ ሺዴ***
***የገንዘብ ሚኒስትር***